# ቃል እንግባ!



ፊት ሳናዞር ለጠላቱ - በቃለ ዜማው ልናምጽ፥
በእንጉርጉሮው እሳተ ሞገድ - ልናር ልንተክን፥
በድምጹ ማዕበል ልንነሳ - ተሰልፈን ልንሻገር፥
ቅዱስ ደሙን ልንቀባ - ክቡር ሥጋውን ልናከብር፤
ሐውልት ልናቆም - የልጅ ምስል ሰንደቅ
የቴዲ እህት ወንድም የሆን  - በዜማው የባረከን፤
ሳለቀሰልን ብላቴና - ለእኛ ሲል ለተሰዋው፤
ቃል እንግባ ለዚህ ወጣት - እንደሌሎች ሳንረሳው::

ግን ወገኔ ንቃ! - ስሙን ለብሰው የሚያታሉ፥
ሳይሆኑ ሚያስመስሉ -  ሜዳ አነሰን የሚሉ፥
ነጋዴዎች ይፈላሉ- በቴዲ ስም ያተርፋሉ፤
ገዳዮች ራሳቸው - በቴዲ ስም ያለቅሳሉ፤
ሽምግልና ምንቴስ - የፖለቲካ ቁማር ይጫዎታሉ፤
ስለስሙ በስሙ - የራስቸውን ተቃዋሚ ያሰልፋሉ፥
ራሳቸው ከራሳቸው ጋር ይደራደሩበታል - ቴዲን ልናስፈታ ይላሉ፤
ከውጭ ሃይሎች ጋት ይሞዳሞዳሉ - አማራጭ መስለው ይወጣሉ::

እንደትናንቱ - ይህ ሁሉ ከንቱ፥
ትጥቅ ማስፈታት ነው ስልቱ፥
እንደገና መግደል ነው ብልሃቱ፥
መከፋፈል ነው አብነቱ::

ስለዚህም ...
ግርዱን ከምርት ልንለይ - አሰላለፋችን ልናሳምር፤
ለመሠሪ አላማቸው ሰለባ ሳንሆን - ለክፍፍል ሳንመቻች፥
ልንጠረጥር - ማንህ? ብለን ልንጠይቅ፥
የነቴዲን ደም ከንቱ ሳናስቀር - በእጅ አዙር መሳሪያ ሳንሆን፤
ማንህ አንተ? ልንለው - አለሁ ባይ አስመሳይን፥
በጊዜ አትራፊ ነጋዴን - መሰሪ ጠላትን፥
        ሳንዘነጋ ለደቂቃ - ቃል እንግባ::

በተግባራዊ ትግል ልንሰለፍ - ሰማእታትን ልናጅብ፥
ፊት ለፊት ልንገጥም - እንደነ ቴዲ  ልንዋደቅ፤
የእውነት ሚዛን ልንመታ - በታሪካችን ሳናፍር፥
ስህተት ካለ ልናርም - ባለፈ ጉድፋችን ሳንሸሽግ፥
በደጎች ላይ ሳናሴር - ከአጥፊዎቻቸው ጋር ሳንሰለፍ፤
የውሸት ክምር ሳንቆልል - የውስጥ አርበኛ ሳንሆን፤
እነቴዲን ልናስፈታ - የሕዝብ ድምጽ ልናሰማ
'ያስተሰርይ' ልንል -  ለክቡር ቃሉ ልንደማ
በቻልነው እንፋለም - በቃ እንግዲህ ቃል እንግባ!!
.....

አመሰግናለሁ
ወልዱ ካሣ